በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የተሳሳተ፣ ተቀባይነት የሌለው ጾም


## መምህር፡ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon@gmail.com


*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ
በየሳምንቱ ረቡዕ ከምሽቱ 12፡30 – 1፡30

## ኅዳር ፬ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# መግቢያ

- ጾም ሁሉ ተቀባይነት ያለው አይደለም። ምክንያቱም እውነተኛ ካለመሆኑ የተነሳ እግዚአብሔር የማይቀበለው ጾም አለና።
- ቅዱስ መጽሐፍም ተቀባይነት ስለሌለው የጾም ዓይነት የሚከተሉትን ምሳሌዎች ይሰጠናል።

1. ***ከሰዎች ውዳሴን ለማግኘት የሚጾም ጾም***

- ጌታችን በተራራው ስብከት ስለዚህ ጾም እንዲህ ብሎናል። "ስትጦሙም፥ እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፤ ለሰዎች እንደ ጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፋሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል። አንተ ግን ስትጦም፥ በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደ ጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ ፊትህንም ታጠብ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል።" *ማቴ 6፡16-18።*
- ከሰዎች ውዳሴን የምንሻበት ጾም ለእግዚአብሔር አይደለም፤እግዚአብሔርም ከዚህ ጾም ጋር ምንም ኅብረት አያደርግምና ጾሙ የተሳሳተ ጾም ይሆናል።

2. ***ትምክህተኞች የሆኑ የፈሪሳውያን ጾም***

- ፈሪሳዊው በእግዚአብሔር ፊት ሊጸልይ ቆሞ ስለራሱ "እግዚአብሔር ሆይ፥ እንደ ሌላ ሰው ሁሉ፥ ቀማኞችና ዓመፀኞች አመንዝሮችም፥ ወይም እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንሁ አመሰግንሃለሁ፤ በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጦማለሁ፥ ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወጣለሁ አለ።"አለ። *ሉቃ 18፡9-14።*
- ይህም ምሳሌ የሚያመለክተን በትሕትናና በተሰበረ ልብ ሳይሆኑ ስለሚጸመው ጾም ነው። ይህም ጾም በእግዚአብሔር ዘንድ የተከለከለ ነው። ምክንያቱም ይህን የሚያደርጉ ሁሉ ራሳቸውን ጻድቅ በማድረግ ሌላውን ይንቃሉና። *ሉቃ 18፡19።*

# የተሳሳተና ተቀባይነት የሌለው ጾም

*3. በተሳሳተ ዓላማ የሚጾም ጾም*

- በአንድ ላይ የተሰበሰቡ አይሁድ የጾሙት ጾም ምሳሌ ይሆነናል፡፡ "በጠባም ጊዜ አይሁድ ጳውሎስን እስኪገድሉት ድረስ እንዳይበሉና እንዳይጠጡ በመሐላ ተስማሙ፡፡" እንዳለ፡፡ *የሐ. ሥራ 23፡12፡፡*
- ይህን ጾም በመንፈሳዊ ሚዛን ጾም ብለን አንጠራውም፤ እነርሱም የጾሙት ይህ ጾም ኃጢአት ነበር፡፡

4. *በነቢዩ በኤርምያስ ዘመን ሕዝቡ የጾሙት የኃጢአት ጾም*

- እግዚአብሔር ይህን ጾም አለመቀበሉን ለነቢዩ ለኤርምያስ እንዲህ በማለት ገልጦለታል፡፡ "እግዚአብሔርም፦ ለዚህ ሕዝብ ስለ መልካም አትጸልይላቸው፡፡ በጾሙ ጊዜ ጸሎታቸውን አልሰማም የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የእህሉን ቍርባን ባቀረቡ ጊዜ አልቀበላቸውም በሰይፍና በራብ በቸነፈርም አጠፋቸዋለሁ አለኝ፡፡" *ኤር 14፡11-12*
- እግዚአብሔር የነዚህን ሕዝቦች ጾማቸውን፤ ጸሎታቸውንና፤ ምጽዋታቸውንም ያልተቀበለው ክፉ ሕይወትን ስለወደዱና በፊቱ ንጹሐን ስላልነበሩ ነው፡፡ ይህም ጾም ያለ ንስሐ ትርጉም አልባ መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ እግዚአብሔር በረሐብ ከጠወለገ ሰውነት ይልቅ ንጹሕ ልብን ይሻል፡፡
- ሰው አንደበቱን ሐሰትን ከመናገር ልቡንም ከኃጢአት ካልከለከለ መጾሙ ዋጋ የለውም፡፡ ሰውነቱን እንኳ ለእሳት አሳልፎ እስኪሰጥ ቢደርስ አያተርፍም፡፡ *1ኛ ቆሮ 13፡3፡፡*

# የተሳሳተና ተቀባይነት የሌለው ጾም…

- ልግስናና ይቅርታን ማድረግ የተለየው ጾም በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም፡፡ እግዚአብሔር ይህን ነጥብ ለነቢዩ ለኢሳይያስ እንዲህ በማለት አስረድቶታል፡፡ "በኃይልህ ጩኽ፥ አትቈጥብ፥ ድምፅህን እንደ መለከት አንሣ፥ ለሕዝቤ መተላለፋቸውን ለያዕቆብ ቤትም ኃጢአታቸውን ንገር፡፡ ነገር ግን ዕለት ዕለት ይሹኛል መንገዴንም ያውቁ ዘንድ ይወድዳሉ ጽድቅን እንዳደረገ የአምላካቸውንም ፍርድ እንዳልተዉ ሕዝብ እውነተኛውን ፍርድ ይለምኑኛል፥ ወደ እግዚአብሔርም ለመቅረብ ይወድዳሉ፡፡ ስለ ምን ጾምን፥ አንተም አልተመለከትኸንም? ሰውነታችንንስ ስለ ምን አዋረድን፥ አንተም አላወቅህም? ይላሉ፡፡ እነሆ፥ በጾማችሁ ቀን ፈቃዳችሁን ታደርጋላችሁ፥ ሠራተኞቻችሁንም ሁሉ ታስጨንቃላችሁ፡፡ እነሆ፥ ለጥልና ለክርክር ትጾማላችሁ በግፍ ጡጫም ትማታላችሁ ድምፃችሁንም ወደ ላይ ታሰሙ ዘንድ ዛሬ እንደምትጾሙት አትጾሙም፡፡ እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ ነውን? ሰውስ ነፍሱን የሚያዋርደው እንደዚህ ባለ ቀን ነውን? በውኑ ራሱን እንደ እንግጫ ዝቅ ያደርግ ዘንድ ማቅንና አመድንም በበታቹ ያነጥፍ ዘንድ ነውን? በውኑ ይህን ጾም፥ በእግዚአብሔርም ዘንድ የተወደደ ቀን ትለዋለህን?  እኔስ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን? የበደልን እስራት ትፈቱ ዘንድ፥ የቀንበርንስ ጠፍር ትለቅቁ ዘንድ፥ የተገፉትንስ አርነት ትሰድዱ ዘንድ፥ ቀንበሩንስ ሁሉ ትሰብሩ ዘንድ አይደለምን? እንጀራህንስ ለተራበ ትቈርስ ዘንድ፥ ስደተኞቹን ድሆች ወደ ቤትህ ታገባ ዘንድ፥ የተራቈተውንስ ብታይ ታለብሰው ዘንድ፥ ከሥጋ ዘምድህ እንዳትሸሸግ አይደለምን?" ኢሳ 58፡1-7፡፡

- በይቅርታና ምሕረት እንዲሁም በንጹሕ ልብ ያልሆነ ጾም አመድ በመነስነስ፤ ማቅ በመልበስ፤ ራስንም ዝቅ በማድረግ ቢጾም እንኳ እግዚአብሔር አይቀበለውም፡፡

# የተሳሳተና ተቀባይነት የሌለው ጾም...

5. *ለእግዚአብሔር ያልሆነ ጾም*

- ዶክተር ስላዘዛቸው የሚጾሙ አሉ:: መልክና ደም ግባት እንዲኖራቸው የሚጾሙ አሉ:: እነዚህ ለእግዚአብሔር አላደረጉትምና ምንም ዓይነት መንፈሳዊ ጥቅም አያገኙበትም::

- ሌሎች ደግሞ ከእግዚአብሔር ወይም ከመንፈሳዊ ዓላማ የተነሳ ሳይሆን ልክ የረሐብ አድማ እንደማድረግ ይጾማሉ:: አንዳንዶችም ምግብን ከተፈጠረባቸው ሥጋዊ ጫና የተነሳ መመገብ ስላቃታቸው እንጾማለን ይላሉ:: እነዚህ ሁሉም ጾም ሆነው አይቆጠሩም::

*በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው ጾም ታዲያ የቱ ነው?*

- ከእግዚአብሔር ጋር ባለን መንፈሳዊ ግኑኝነት ላይ ተመሥርቶ፤ እግዚአብሔር በሕይወታችን መኖሩ እየተሰማን የሚጾም ጾም ነው::

- በእያንዳንዱ እንቅስቃሴዎቻችንነ ወይም ድርጊቶታችን እግዚአብሔር የሚነበብበት የተመረጠ የመሥዋዕትነት ጊዜ ነው::

- በምንጾምበት በእያንዳንዱ ቀን ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግኑኝነት እየጠበቀ፤ እያደገም ሄዶ ጾሙ እንዲረዝምና መጨረሻም የሌለው እንዲሆን እስክንመኝ ድረስ የሚያደርሰን ነው::

# ቅዳሴ በማስቀደስ

# እንዳንጠቀም የሚያደርጉን

# ምክንያቶች

# ቅዳሴ በማስቀደስ እንዳንጠቀም የሚያደርጉን ምክንያቶች

- ቅዳሴ ቃሉ የግዕዝነው:: ፍቺውም ምስጋና ማለት ነው:: ካህናት በቤተ መቅደስ ሥጋውና ደሙ የሚያደርሱት የጸሎት ሥርዓት ቅዳሴ ይባላል። በቅዳሴ መላእክት ሁሉ በመንበሩ ዙሪያ ረበው ይገኛሉ። በቅዳሴ ሰዓት የምናሳልፈው ጊዜ በሰማይ ካለው ጥቂት ጊዜ ወስዶ በምድር እንደማሳለፍ ይቆጠራል። በሥጋ ስለሆንን ይህ ሁልጊዜ ከዓይናችን ተሰውሮአል። ብዙዎች ግን ይህንን ክብር አይተው ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።

- በቅዳሴ የምናገኘውን ጥቅም እንዳንረዳ የሚያደርገን ምንድር ነው?

1. *ወደ ቤተክርስቲያን ዘግይቶ መምጣት*

- ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን ዘግይተው የሚደርሱ ከሆኑ ቅዱስ ቁርባኑን መቀበል፣ የተነበበውን ወንጌል መስማት፣ መልካሙን የምስጋና ዜማ፣ በቅዳሴ ሰዓት የሚደረገውንና የሰውንም ልብ ወደ ሰማይ የሚያደርሰውን ጥልቅ ጸሎት መሳተፍ አይችሉም። ስለዚህም ነው ጌታችን በማለዳ ወደ ቤተ ክርስቲያን እንድንገሰግስ የሚመክረን። "እኔ የሚወድዱኝን እወድዳለሁ፥ ተግተው የሚሹኝም ያገኙኛል::" *ምሳሌ 8:17::* "ነገም የተዘጋጀህ ሁን፥ በማለዳም ወደ ሲና ተራራ ወጥተህ በዚያ በተራራው ራስ ላይ በፊቴ ቁም::" *ዘጸአ 34:2::* "በማለዳ ድምፄን ትሰማለህ፥ በማለዳ በፊትህ እቆማለሁ፥ እጠብቃለሁም::" *መዝ 5:3::* "ማለዳም ተነሥቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ ወደ ምድረ በዳም ሄዶ በዚያ ጸለየ::" *ማር 1:35፤ ዮሐ 8:2::*

# ቅዳሴ በማስቀደስ እንዳንጠቀም የሚያደርጉን ምክንያቶች…

2. *<u>በቅዳሴ ተሰጥዖ አለመሳተፍ</u>*

- ማለዳ ብንደርስም እንደ ተሳታፊ ሳይሆን እንደ ታዛቢ የምንቆም አለን፡፡ በቅዳሴ ሰዓት የሚገኙ ሁሉ የቅዳሴው አስፈላጊ አገልጋዮች ናቸው፡፡ ቄሱ አግብርቲከ እለ ተልእኩ ብሎ የሚያነሳው ሁሉን ነውና፡፡

- በቅዳሴ ሰዓት ሁሉም ተሰጥዖውን በፍጹም ነፍስና፤ ልብና ስሜት ሆኖ በመቀበል እግዚአብሔር የሚሰጠንን ሰማያዊ መደላደልና ሰላም መቀበል ይጠበቅብናል፡፡ "በዕጣንም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ቆመው ይጸልዩ ነበር፡፡" *<u>ሉቃ 1፡10፡፡</u>*

3. *<u>ተሰጥዖውን ስንቀበል ጥልቅ ትኩረትን መንፈግ ወይም ትርጉሙን አለመረዳት</u>*

- ብዙ ጊዜ ተሰጥዖውን ትርጉምን ተረድቶ በተመስጦ ልብ በማለት ሳይሆን በልምድ መመለስ ይታይብናል፤ ይህም በቅዳሴ ሰዓት ፍጹም አትኩሮትን እንድናጣ ያደርገናል፡፡

- "እንግዲህ ምንድር ነው? በመንፈስ እጸልያለሁ በአእምሮም ደግሞ እጸልያለሁ፤ በመንፈስ እዘምራለሁ በአእምሮም ደግሞ እዘምራለሁ፡፡" *<u>1ኛ ቆሮ 14፡15፡፡</u>*

# ቅዳሴ በማስቀደስ እንዳንጠቀም የሚያደርጉን ምክንያቶች…

4. *በቅዳሴ ሰዓት ከመንፈሳዊ ነገሮች ይልቅ በሌሎች ሥራዎች መጠመድ*

- በቅዳሴ ሰዓት አንዳንዶች አስተዳደራዊ (የተለያዩ ነገሮችን መሸጥ)፣ ስጦታዎችን (መባዕ) ወዘተ በመቀበል፣ ሌሎች ደግሞ በወሬ፣ የተለያዩ ጥናቶችን በማከናወን ይጠመዳሉ። ይህም ቅዳሴውን ከመስማትና ተሰጥዖውንም ከመቀበል ይከለክላል።

- ጌታችን "ሌላውን ሳትተዉ ይህን ልታደርጉት ይገባችሁ ነበር።" *ሉቃ 11:42።* "ለሁሉ ዘመን አለው፥ ከሰማይ በታችም ለሆነ ነገር ሁሉ ጊዜ አለው።" *መክ 3:1።* "በተስፋ ደስ ይበላችሁ፤ … በጸሎት ጽኑ።" *ሮሜ 12:11።*

5. *ግዕዝ ስለሆነ አንሰማውም ማለት*

- በቅዳሴ ሰዓት የሚባለው ሁሉ በግዕዝ ስለሆነ አንረዳውም የሚሉ አሉ።

- ግዕዝ የጥንት ቋንቋችንና ቅርሳችን ነው። ግዕዝ የአባቶቻችንና አያቶቻችን ቋንቋ ስለሆነ ይልቁኑ ልናጠናው ይገባል። ለሁሉም የጋራ የሆነ የምስጋና ቋንቋችን ግዕዝ ነው። "ልጄ ሆይ፥ የአባትህን ምክር ስማ፥ የእናንትህንም ሕግ አትተው።" *ምሳሌ 6:20፤ 1:8።*

# ቅዳሴ በማስቀደስ እንዳንጠቀም የሚያደርጉን ምክንያቶች…

6. *ቅዱስ ቁርባን አለመቀበል*

- ቅዱስ ቁርባን በመቀበል ሕይወት ይቀደሳል፣ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 6 ቁጥር 46 ጌታ እንደተናገረው ከርሱ ጋር እንዋሐዳለን፣ ከክፉ ነገር ሁሉ እንርቃለን፣ በአጠቃላይ ሰውነትን ሁሉ ይጸዳል፣ ይጣፍጣል በረከትን ያገኛል።

- አንዳንዶች ቅዳሴ ማስቀደስ እንዲሁ ልማድ ሆኖባቸው አስቀድሰው ቅዱስ ቁርባን ሳይቀበሉ ወራትና ዓመታት ያልፋሉ።

- ቤተክርስቲያን ንስሐ ገብተው የተዘጋጁትን ሁሉ "እንካችሁ፥ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ።… ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ።" እንዳለ ከቅዱስ ቁርባን እንዲቀበሉ ትመክራለች። *ማቴ 26፡26-27።*

- ቅዱስ ቁርባንን የማይቀበሉ ሁሉ ከአማንያን አንድነትና ኅብረት እንዲሁም ከታላቁ በረከት ራሳቸውን ያርቃሉ።

7. *ንስሐ ሳይገቡ ቅዱስ ቁርባንን መቀበል*

- ሰው ንስሐ ሳይገባ ቅዱስ ቁርባን ሊቀበል ሊመጣ ይችላል። ያልተናዘዙትንና ያልተውትን ኃጢአት ባሰቡ ቁጥር ይህ ስሜት ከመንፈሳዊ በረከት ከመሳተፍ ያርቃል፤ ከምስጢራተ ቤተ ክርስቲያን የሚሳተፍ ሰው ንስሐ የገባ የተዘጋጀ መሆን ይገባዋልና።

***አምላካችን እግዚአብሔር እንደ ፈቃዱ ጾመንና አስቀድሰን ከሚያድለው በረከት ዘወትር ተሳታፊ ያደርገን ዘንድ ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን። አሜን።***

ወስብሐት ለእግዚአብሔር፡፡

ይቆየን፡፡